# ባልበላውም ጭሬ ልድፋው ባዩ ጽንፈኛ ዲያስፖራ

አስራት 04/30/13

የዲያስፖራ አባላት በተለያየ ምክንያት ከኢትዮጵያ ወደ ተለያዩ የውጭ ሃገራት በዋናነትም ወደ አሜሪካና ጥቂት የአውሮፓ ሃገራት በመሄድ ኑሮአቸውን በዚያው ያደረጉ ዜጎች ናቸው። አብዛኞቹ ዲያስፖራዎች በስደት በሄዱባቸው ሃገራት ዜግነት ያገኙና ጥረው ተጣጥረው ሕይዎታቸውን የሚመሩ፤ ሌሎችም ሀብትና ንብረት አፍርተው ቤተሰብ የመሰረቱ፤ በትምህርትም ልቀው በተለያየ መስክ ተሰማርተው ተከብረው የሚያስከብሩ ሀገርና ወገንን የሚያኮሩና የሚያስጠሩ ሆነው ሃገራቸውንና ወገናቸውን በተለያዬ መልኩ እየጠቀሙና ለሃገር ልማት ከፍተኛ አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ ያሉ ናቸው፡፡

ያካበቱትን እውቀትና ልምድ እንዲሁም ሀብት ወደ ሀገራቸው በማምጣት በተለያየ የኢንቨስትመንት መስክ እየሰሩ ያሉ እዛም ሆነው ያፈሩትን ሀብት ይዘው ኢትዮጵያ መጥተው ለመስራት የወሰኑም ተዘጋጅተው የሚገኙም አሉ፡፡ እነዚህ ለሀገራቸውና ለወገናቸው የመጠቀ ፍቅር ያላቸውና የሀገራቸውን ውለታ ምን ሰርተን እንመልስ ብለው የሚጨነቁ የሚጠበቡ ናቸው፡፡ ከዚህ ውጭ ያለውና በጽንፈኛ ተቃዋሚነት ጎራ ተሰልፎ በፈረንጂ ፒያሳና አደባባይ አታሞ እየደለቀ የሚጮህ፤ በየፓልቶኩና ማህበራዊ ድረ ገጽ ላይ በባዶው የሚያቅራራና ጠያቂ ሕግ የለብኝም እያለ የሚያንቧችር፤፤መሬት አልበቃው ብሎ እንደ ፊጋ በሬ ሲጎደፍር የሚውል አለ፡፡ አጥፍቶ ጠፊን የሚመስለው ጽንፈኛው ዲያስፖራ ማለት ይሄ ነው፡፡

በ1997 የተካሄደውን ምርጫ ተከትሎ የተቋቋመው ቅንጅት የተባለው የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት ስብስብ አመራሮች ታስረው ለፍርድ መቅረባቸውን ተከትሎ በነዚህ ዙሪያ የነበሩ የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት ወደ ተለያዩ ሀገራት ሄደዋል፡፡ የታሰሩት የቅንጅት ከፍተኛ አመራሮችና አባላት የፍርድ ሂደት ውሳኔው እንዳለ ሆኖ እንዲሁም ታስረው የተለቀቁ የግል ጋዜጠኞች በሽምግልናና በምህረት እንዲለቀቁ ከተደረገ በኋላ ወደ አሜሪካና አውሮፓ አንዳንድ ከተሞች ገብተዋል፡፡ ግንቦት ሰባት የተባለውን ድርጅት ኢሳት

የተባለውን ሳተላይት ቴሌቬዥን አቋቁመው እየሰሩ ያሉትም የግል ጋዜጠኞች የነበሩት ናቸው፡፡

በአጠቃላይ ሲታይ በአሁኑ ጊዜ ቁጥሩ ከ750 ሽህ የሚልቅ ኢትዮጵያዊ በአሜሪካ እንደሚኖር መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ጽንፈኛና አክራሪ የሆነው በፖለቲካ መስመሩ የተለያየውና በአመለካከት የማይገናኘው የዲያስፖራ አባላት ግን አጋጣሚው በአንድ ሀገር ያገናኛቸው እንጂ የዘይትና ውሃ ቅልቅል ያህል በመካከላቸው የሰፋ ልዩነት ያላቸው ከመሆኑ የተነሳ የየራሳቸውን ግላዊና ቡድናዊ ፍላጎት ይዘው በጭፍን ተቃውሞና በጥላቻ ስሜት ብቻ የሚነዱ ናቸው።

አንዳንዶቹም በቀላሉ ጥገኝነት አግኝተው ሕይወታቸውንና ኑሮአቸውንም ለመለወጥ በማሰብ ብቻ በሚያሳፍር መልኩ "በፖለቲካ ምክንያት" ተሰደድን ብለው ከሃገር የወጡ ናቸው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም አንዳንድ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ሃሰተኛ የአባልነትና ሌሎች ደጋፊ መረጃዎችን አዘጋጅተው በመስጠትና ከዚህም ባለፈ በገንዘብ በመሸጥ ሲነግዱበትና ሲያተርፉበት እንደነበር በርካታ ማስረጃዎችን ማቅረብ ከባድ አይሆንም። ሌሎችም ከሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ተሳትፎ ይልቅ በአመጽ፣በሁከትና በሽብር መንገድ በአቋራጭ ሥልጣን ለመያዝ ካላቸው ምኞት አንጻር አገር ቤት ለዚህ እንቅስቃሴአቸው አላመች ሲላቸው አገር ጥለው የኮበለሉ ናቸው።እዛም ሄደው በአገር ቤት ሲያደርጉት የነበረውን ዓይነት ሴራ በስደተኛው መሀል ሆነው መጎንጎናቸውን ገፍተውበታል፡፡ ይህን የመሰለ እጅግ በጣም በመሰረታዊ የፖለቲካ አመለካከቱ የሰፋ ልዩነት ያለው ክፍል የየራሱን ግላዊና ቡድናዊ ምክንያት መነሻ በማድረግ ነው የጥላቻ ጦር እየሰበቀ ያለው፡፡

በደርግ ዘመን መኢሶን ሆነው በከፍተኛ ደረጃ የኢሕአፓ አባላትን ሲያስሙቱ የነበሩትም ሰዎች በስደት ቀድመው አሜሪካን ከገቡት የኢሕአፓ ሰዎች ጋር እዛው አሜሪካ ነው የሚገኙት፡፡ በተለይ በሁለቱ በኩል ይካሄድ የነበረው የከረረ የመጠፋፋት ትግል የኢትዮጵያን የፖለቲካ ባህል እጅግ በከፋና አደገኛ በሆነ መልኩ መርዞትና በክሎት ሂዷል፡፡

ያ ትውልድ በመባል የሚጠራው ክፍል በመሰዋእትነት ጠንካራ የመሆኑን ያህል በዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት፣ ልዩነትን ተከባብሮ በመቻቻልና በመጠበቅ፣ የተለየ ሀሳብን

ለማስተናገድ በሮቹ ዝግ መሆናቸው፤ ከእኔ ወይንም ከእኛ የተለየ የፖለቲካ አመለካከት ያለው ወዳጅ ሳይሆን ጠላት ነው፤ መጥፋት አለበት ብሎ ማመኑ፤ በዚህም በፖለቲካ አመለካከት ልዩነት የድሀ ልጅ መግደልና ማስገደል ድረስ  መሄዳቸው ተራውን ዜጋ ሁሉ ማጥፋታቸው መለያ ባሕርያቸው  ነበር፡፡

በወቅቱ በየፊናቸው ወግነው ያወድሱት የነበረው የቦልሼቢኮችና የሜንሺቪኮቸ የእርስ በእርስ መተላለቅ፤ በሌኒንና ትሮስኪ መካከል የነበረው ትግል  ኢትዮጵያም እንዲመጣ ብዙ ታግለዋል፣ ተሳክቶላቸዋልም ፡፡ትሮትሰካይቶች ብለው የሚጠሩዋቸው በኢትዮጵያ የፖለቲካ ትግልም ውስጥ ነበሩ፡፡ ከእነሱ ተቃራኒ ርዕዮተ ዓለም ያለው መብቱ መሆኑ ተረስቶ መጥፋት አለበት፣ መሞት አለበት ብለው ገርፈው አስገርፈዋል፣ገድለው አስገድለዋል።፡፡ የእነሱ ስር የሰደደ የመጠላላትና የጥላቻ ፖለቲካ በሽታና መርዝ ኢትዮጵያን በክሎአትና መርዟት አለፉ፡፡ ጦሱ ለተተኪውም ትውልድ አለፈ፡፡

ዛሬ በዓለም ላይ የኮሚኒስት ስርዓትና አመለካከት በመዳከሙ የተነሳ በስደት በሄዱበት አገር የፖለቲካ አቋማቸውን ገልፍፈው ቀይረው ሊበራል  ነን ፤ኒዮ ሊበራሊዝም ነን፤ ሶሻል ዲሞክራት ነን ፤ነጻ ገበያ ፤ነጻ ፕሬስ፣ በነጻ ተቋማት በሕግና የበላይነት በሰብአዊ መብት መከበር፤ በመንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች መኖርና መስፋፋት እናምናለን ፤ምዕራቡ ዓለም ሊደግፈን ይገባል እያሉ በተለያየ ጎራ ተደራጅተው የሚያምሱት፤ ሰውንም በጥላቻ ባህር እንዲሰምጥ የሚያደርጉት እነዚሁ የቀድሞዎቹ ጉምቱ ፖለቲከኞች ናቸው፡፡

ኢሕአፓም መኢሶንም በኋላ የተወለደው ኢሰፓም የኮምኒስታዊ መርህ ተከታዮች ሲሆኑ ኢሰፓን በማቋቋምና በማስተማሩ ረገድም ቁልፍ ሚና የተጫወቱት ከኢሕአፓና ከመኢሶን የተመለሱትና ደርግን የተቀላቀሉት ሰዎች ነበሩ፡፡ በስተኋላ ላይ እስከዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ ውጭ በሙሉ የተመሰረቱትን የተቃዋሚ ፓርቲዎች ኢድህቅ ይሁን መድህን ኢዴፓ ይሁን መኢአድ ወይንም አንድነት፤ ጥምረት ይሁን ሕብረት፤  ቅንጅት ይሁን መድረክ፣ ወይንም ግንቦት ሰባት በአንዱ ወይም በሌላው እነሱ የሌሉበት ምንም ነገር የለም፡፡

በትልቁ በሀገሪቷና በሕዝቧ ላይ ጉዳት እያስከተለ ያለው ወደ ፊትም አደጋ ሆኖ የሚታየው የከረረ የጥላቻና  የጎሳ ፖለቲካን ማራመድ ሲሆን፤ ምንም በጎ ነገር አልተደረገም፤ብሎ መደምደምና መካድ ሁሉም ዜጋ በሀገሩ ጉዳይ ባለቤትና ድምጹን የማሰማት፤ ሃሳቡን

የመግለጽ፤ ቢያንስ የመደመጥም መብት አለው የሚለውን መርህ በመርገጥ እኛ ብቻ ትክክልና አዋቂ ነን፤ ከእኛ ውጪ ያለው ለሀገሩ ለወገኑ አያሰብም፤ ለሆዱ ያደረ ፤የተገዛ ነው ብለው የሚያስቡ ናቸው፡፡

በጠረጴዛ ዙሪያ ልዩነትን መፍታት፤ የመደማመጥና በሚያግባባ የጋራ ጉዳይ ላይ መግባባት፣ በሚያለያይ ደግሞ ተከባብሮ መለያየት ሳይሆን ፤በስድብ በዘለፋ፤ በስም ማጥፋት፤በአመጽና ሁከት አልፎም በሀይልና በጡጫ የሚያምኑ እጅግ በጣም ኋላቀር ፤ያልተገራና ያልሰለጠነ ፤ ጥፋትንና ውድመትን ብቻ እንደ መፍትሔ የሚያዩ፤ በከፋ የበቀል ፖለቲካ ውስጥ የተዘፈቁ ሰዎች በጽንፈኛ አክራሪ ፖለቲከኛነት መቆማቸው መቼም ሆነ መቼ ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ የተሻለ ቀን ያመጣሉ ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው፡፡

መጀመሪያ ነገር ለጭፍን ጥላቻ ፖለቲካ ዋነኛ ምክንያት ከሆነውና ደማቸው ውስጥ ከሰረጸው ጸረ ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብና ድርጊት  መቼ ተላቀቁና ነው፤ ዛሬ ለሃገርና ለሕዝብ ዋነኛ ተቆርቃሪ መስለው ለመታዬት የሚፋትኑት?

ፍላጎታቸው የፖለቲካ ስልጣን ምኞታቸውን በሕገወጥና አቋራጭ በመሰላቸው ማንኛውም የአመጽና የሁከት ሥልት ማሳካት ብቻ ነው። ሕዝቡን ለአንተ ስንል ነው "ትግል" ውስጥ የገባነው ይሉታል። እናንተ እነማናችሁ? የፖለቲካ ፕሮግራማችሁና ስትራቴጂያችሁ፣ዓላማችሁና ፖሊሲያችሁ ምንድነው? ቢባሉ የሚያቀርቡት አንዳችም ተጨባጭና አሳማኝ ነገር የላቸውም።በዚህ ረገድ ሌላው ቀርቶ አሜሪካን ሀገር ያለውና ይደግፈናል የሚሉት ጥቂት  ዲያስፖራ እንኳ በቅጡ አያውቃቸውም፡፡  ለነገሩ የእነሱን ክፋት፣ መሰሪነት፣ የስም ማጥፋት የፈጠራ ውንጅላና መጠፋፋት፣ ሌላውን ንጹህና ሰላማዊ ዜጋ ጨምሮ እርስ በርሳቸው መወነጃጀልና መዘላለፍ፣መጠላለፍ፤ ሀገርንና ትውልድን ለውድቀት ያበቃ  ገዳይ ባሕርያቸውን ባያውቀው ይመረጣል አይጠቅምምና፡፡ እንግዲህ የአክራሪው ጽንፈኛ ዲያስፖራ የተቃዋሚ ሀይሎች አሰላለፍና የተፈጥሮ  ኬሚስትሪያቸው ቁልጭ አድርጎ የሚያሳየን እውነት ይሄንን ነው፡፡

በአገር ቤት እያሉ በየነበሩበት የሲቪልም ሆነ የወታደር መ/ቤት በከፋ አምባገነንነታቸው የሚታወቁ፤ በስንቱ ሕይወት የቀለዱና የተጫወቱ፤ የስንቱን ትዳር ያፈረሱና ሕጻናትን የበተኑ ፤የአገርና የሕዝብ  ሀብትን ዘርፈውና ጭነው የወጡ፤ ባልን አስረው ወይንም ገድለው ሚስት የወረሱ፤ ስንትና ስነት ዘግናኝ ታሪክና ጉድ በጀርባቸው የተሸከሙና

ከሕሊና ወቀሳ ነጻ ያልሆኑ ወንጀለኞች ዛሬ ላይ አፈፍ ብለው ተነስተው ለአገር ተቆርቋሪ ለሕዝቧና ለባንዲራዋ ተሟጋችና፣ የዲሞክራሲና የሰብአዊ መብት ብሎም የፕሬስ ነጻነት ተከራካሪ ነን ሊሉ አይችሉም። ነገሩ ሁሉ "ጅብ የማያውቁት ሀገር ሄዶ ቁርበት አንጥፉልኝ አለ" እንደሚባለው ነው የሚሆነው፡፡

ልክ ነው አብዛኛው ዲያስፖራ የኋላ የጎደፈ ታሪካቸውን በውል ላያውቀው ይችላል። በተለይ ወጣቱ ደግሞ የእድሜ አቻዎቹም ስላልሆነ የዛን ዘመኑን እኩይ ምግባራቸውን አላየም። የሆነ ሆኖ በማንኛውም የቤተሰብ አባል ላይ ግን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ያደረሱት በደል ጠባሳው አሁንም ድረስ የሚታወስ ነው። የእነዚህ ጉዶች ታሪክ በአጭሩ "ለማያውቅሽ ታጠኚ" የሚባለውን ሀገርኛ አባባል ያስታውሰናል፡፡

በየፓልቶኩ ውይይታቸው ለሚሰጡት አስተያየትና ለሚሰነዝሩት ቃል እንኳን ትንሽ ኢትዮጵያዊ ባህልና ጨዋነት አይታይባቸውም፡፡ መረንና ያልተገራ፣ አበቃቀል እንዳላቸው የሚያሳይ ነው፡፡ ጽንፈኛው ዲያስፖራ አክራሪ የፖለቲካ ሀይልና በስሩ የተኮለኮለው አጫፋሪ ስለኢትዮጵያና ስለኢትዮጵያዊነት ሲያስብ ኢትዮጵያዊነት ማለት ነብር ዝንጉርጉር እንደሆነው ሁሉ ልዩነቱን ጌጡ በማድረግ ዘርና ሀይማኖት ሳይለይ አብሮ የኖረና ዛሬም ድረስ የዘለቀ አስተዋይነትንና መቻቻልን ያዳበረ መሆኑ መዘንጋት የለበትም፡፡

እነዛ የጥንት አባቶች የሀገር ፍቅርን የመሪነት ጸጋን ማስተዋልን ብልህነትንና ጥበብን ከሚታመኑለት ፈጣሪ ተሰጥቶአቸው ወይንም ታድለውት ሰርተውበት አልፈዋል፡፡ የሽማግሌዎች ምክርና ተግሳጽ የሚሰማባትና የሚደመጥባት ሀገር ነበረች ኢትዮጵያ፡፡ እነሱ እንደ ዛሬው ትውልድ ዲግሪ ማስትሬት ዶክትሬት አልነበራቸውም፡፡ የየል ወይንም የኦክሲፎርድ ዩኒቨርሲቲ ምሩቃንም አልነበሩም፡፡ የሀገራቸው ገዳማትና መስጊዶች ምሩቆች፣ ፈሪሀ እግዚአብሔር የነበራቸው አስተዋዮች ነበሩ፡፡ በጥላቻ መዋጥ፣በስሜት እየተነዱ መንተክተክ፣ በበቀል ጋሪ መጋለብ አገር እንደሚያጠፉ ትውልድ እንዲሚቀጥፍ ስለሚያውቁ ሁሉንም በፍቅርና በእኩልነት ዳኝተው፣ በቀልና ደም መፋሰስ እንዳይኖር ታግለውና ለሀገር ሰላምና እድገት ሰርተው አልፈዋል፡፡

በዲያስፖራ ያለው ጽንፈኛና አክራሪ ሀይል ከቀደሙት ኢትዮጵያውያን አባቶቹ ብዙ ሊማር ይገባዋል፡፡ ጥላቻን እየዘራና የጥላቻ እሳት እየቆሰቆሰ፣አገርና ትውልድ እንዲጠፉ፣

የበቀል ዛር ወርዶ ሕዝብ እንዲፈጅ ለማድረግ እየሄደበት ያለው መንገድ መገታት አለበት፡፡ ሀገር ካለ ሕዝብ፣ሕዝብም ያለሃገር ትርጉም የለውምና፡፡